ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

ጥር 2006 ዓ.ም. የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች ቁጥር 31

# ከሠል በኢትዮጵያ

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በሻሸመኔ ፋና ኤፍ. ኤም (በ103.4 ሞገድ) ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

ኢሜይል: fss@ethionet.et

ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ በዓለም በከፍተኛ የእንጨት ከሠል ምርት ከሚታወቁ አገሮች አንዷ ስትሆን እንደ አለም አቀፍ የምግብና እርሻ ድርጅት ጥናት መሠረት በሀገሪቱ እ.ኤ.አ ከ2000-2009 ባሉት 10 ዓመታት ውስጥ ከ 32 ሚሊዮን ቶን በላይ ከሠል እንደተመረተ ተመልክቷል። ይህም በዓመት 3.2 ሚሊዮን ቶን መሆኑ ነው። የከሠል ምርትና አጠቃቀም በእስያና በላቲን አሜሪካ እየቀነሰ፤ በአፍሪካ ደግሞ እየጨመረ የመጣ ሲሆን አሁን በአህጉሪቷ በሚታየው የህዝብና የከተሞች ዕድገት ሁኔታና የኢኮኖሚ መነቃቃት ሳቢያ የኃይል ፍላጎት ማደግ መከተሉና የከሠልም ምርትና ፍጆታ እየጨመረ መምጣቱ የሚያጠያይቅ አይሆንም።

ከሠሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች 81 በመቶ የሚሆነው ህዝብ የማገዶ ፍጆታውን ከደንና ከእርሻ ውጤቶች ያገኛል። ይህ አሀዝ በኢትዮጵያ እስከ 92 ከመቶ ይደርሳል። በሀገራችን ከእንጨትና ከከሠል በተጨማሪ የከብቶች ኩበት፣ የእርሻ ተረፈ-ምርቶች፣ የእንጨት ፍቅፋቂ፣ የቡና ፍልፋይ፤ ቅጠላ ቅጠሎች ጭምር በሰፊው ለኃይል ምንጭነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ከሠል ለብዙ የህብረተሠብ ክፍል የስራ መስክና ዋነኛ የኃይል ምንጭ ቢሆንም፤ አመራረቱ፣ ግብይቱና አጠቃቀሙ ከፍተኛ አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ችግሮች ይስተዋሉበታል።

ከሠል በቤት ውስጥ ምግብ ለማብሰል፣ ቡና ለማፍላት፣ በቆሎ ለመጥበስ፣ ልብስ ለመተኮስ ሲያገለግል ዛሬ ዛሬ በመንገድ ዳር ጀበና ጥደው 'ኑ ቡና ጠጡ! ለሚሉት፣ ለመሸበት ከተሜ ፓስቲና በቆሎ እሸት እየጠበሱ ለሚያቀርቡት ተንቀሳቃሽ ምግብ አቅራቢዎች ከሠል ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣል።

በከተሞችና በገጠር መንደሮች የሚኖሩ የእጅ ሙያ ጥበበኞች ለምርት፣ ለቤት ውስጥና ለጦር መሳሪያነት የሚያገለግሉ የብረት ውጤቶችን ለማምረት፤ የወርቅና የብረት አንጥረኞች ጌጣጌጦችን ለመቅረፅ ከሠልን በሠፊው ይጠቀማሉ። ይህ ጠቃሚ የኃይል ምንጭ እንዴት፣ የትና በማን ይመረታል? የገበያ ትስስሩ ምን ይመስላል? ምን ችግሮችን አስከትሏል? የሚሉና መሠል ጥያቄዎችን በማንሳት፤ መንግስት፤ ማህበረሰቡና ግለሠቦች ምን የፖሊሲና የተግባር አቅጣጫዎች መከተል እንደሚገባቸው መጠቆም ተገቢ ይሆናል።

## 2. የጥናቱ ዓላማዎችና ዘዴዎች

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ከላይ ከተመለከቱት ችግሮች በመነሳት በ2005 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የከሠል ምርትን፤ ስርጭትን፣ ግብይትና አጠቃቀምን የሚመለከት አንድ ጥናት አካሂዷል። የጥናቱም አላማዎች፤ በአገሪቱ የከሠል አመራረት፣ ግብይትና አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መገምገም፤ የከሠል ምርትን አካባቢያዊ፣ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች መዳሰስና፣ የከሠል አመራረትና ንግድ አካባቢን በማይጎዳና በዘላቂነት እንዲካሄድ የሚያስችሉ የፖሊሲ ኃሳቦችን መጠቆም ሲሆን፤ የጥናቱ ዘዴዎች ከሠል በማምረት፣ በማጓጓዝና በመነገድ ስራ ላይ ከተሠማሩ ግለሠቦችንና ተጠቃሚዎች፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ቃለ-ምልልስ (Interview) ማድረግን፤ በአዲስ አበባ ከተማ የከሠል አቅርቦትን የናሙና ቆጠራ (survey) ማካሄድና፤ በዋና ዋና ከተሞች የዳሰሳ ምልከታዎችን ማድረግን፣ በኢትዮጵያና በሌሎች አገሮች የተሠሩ

ጥናታዊ መረጃ ዎችን መገምገምን ያካተቱ ናቸው።

## 3. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### 3.1 ከሠል ከምን፣ እንዴት፣ የትና በማን ይመረታል?

በሀገራችን ከሠል በዋነኛነት ከእንጨት የሚመረት ሲሆን በእጅጉ ተፈላጊ የሆነው የከሠል ዓይነት ከግራር ዛፍ የሚመረተው ነው። በመቀሌ፣ በባህርዳር፣ በድሬድዋ፣ በአዋሽ/ገዋኔ፣ በሀዋሳ፣ በላንጋኖ፣ በብላቴና በአርባምንጭ ከተሞች በተደረገው የዳሰሳ ጥናትና ሌሎች መረጃዎች መሠረት፤ በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍል የሚገኙ ከሠል አክሳዮች የተለያዩ የዛፍ ዓይነቶችን የሚጠቀሙ ሲሆን በዋናነት ግራር፣ አባሎ፣ ዋንዛ፣ ሰሳና፣ ጥድ፣ ፕሮሶፒስ፣ ቀንጥር፣ ብሳና፣ ባህር ዛፍ፤ የመሳሰሉ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ይገኙበታል። ከሠል እነጨት-ነክ ካልሆኑ ነገሮችም፤ ለምሳሌ ከእርሻ ተረፈ-ምርቶች፣ ከእንጨት ፍቅፋቂ፣ ከጥጥ ፍሬ፣ ከቡና ገለባና ከመሳሰሉት ሊዘጋጅ ይችላል።



የአፋር፣ የኦጋዴን፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጋሞ ጎፋ፣ የቦረና፣ የመተማ፣ የሑመራና እንዲሁም ሀገሪቷን ለሁለት ከፍሎ ከደቡብ እስከ ሰሜን ምስራቅ የተዘረጋው የስምጥ ሸለቆ መካከለኛ ክፍል፤ ሞጆን፣ አዳማን፣ አዋሽን፣ ድሬዳዋን ይዞ እስከ ጅቡቲ የሚዘልቀው ሜዳማ አካባቢ ዋነኛ የከሠል ምርት ምንጭ ሆኖ ቆይቷል፤ ዛሬም ነው። እነዚህ ስፍራዎች ግራርን ጨምሮ የተለያዩ ዕፅዋቶች የሚገኙባቸውና በከፍተኛ ሙቀት ሥር ያሉ፤ ብዙ ጊዜም የዝናብ እጥረት የማይለያቸው ለድርቅ የተጋለጡ ስፍራዎች ናቸው።

እነዚህ በተፈጥሮ ብቻ የበቀሉ ዛፎች የሚገኙባቸውና ምንም ዓይነት የተደራጀ የደን ልማት የማይካሄድባቸው ስፍራዎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ አርብቶ-አደሮችና ከፊል አርብቶ-አደሮች የሚኖሩባቸው፤ እጣን፣ ከርቤ፣ የዱር ሙጫና አብዛኛው ከሠል የሚመረትባቸው ቦታዎች ሲሆኑ ሠፋፊ እርሻዎችም የሚገኙባቸውና በከፍተኛ ጫና ስር የሚገኙ አካባቢዎች ናቸው።

በታዳጊ አገሮች ውስጥ ከደን በሚገኝ ገቢ የሚተዳደሩ ሰዎች ከሚኖሩበት ሕብረተሰብ የኑሮ ደረጃ የመጨረሻው እርከን ላይ የሚገኙ ናቸው። በባህላዊ መንገድ ጣውላ በማውጣት፣ የማገዶ እንጨት በመሸጥ፣ ከሠል በማክሰል፣ እጣን፣ ከርቤና የዱር ሙጫ በመሰብሰብ፣ ቅመማ ቅመሞችን ከጫካ በመልቀምና በመሳሰሉት ስራዎች ኑሩዋቸውን የሚገፉ ሰዎች ቁጥር በቀላሉ አይገመትም። በተለይ ከሠል በማክሰል ስራ ላይ የተሠማሩ ሠዎች በአብዛኛው የስራ አማራጭ በማጣት ብቻ በዚህ የስራ መስክ ለመተዳደር የተገደዱ ሰዎች መሆናቸውን ራሳቸው ያረጋግጣሉ። በየአካባቢው የሚገኙ አብዛኛዎቹ አክሳዮች ህጋዊ ካለመሆናቸው የተነሳ ቁጥራቸውን በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ነው።

ባሕላዊው የአከሳሰል ዘዴ እንጨቱን መሬት ላይ አደራርቦ በመከመር በሳርና ቅጠላቅጠል ከሸፈኑ በኂላ አየር እንደልብ እንዳይገባ በአፈር ሸፍኖ ለመለኮሻ በተተዉ ሁለትና ሶስት ቀዳዳዎች በኩል ክምሩ በመለኮስ የሚካሄድ ነው። አየር በብዛት ገብቶ እንጨቱ ነድዶ ወደ አመድነት እንዳይለወጥ በትኩረት መከታተል ተገቢ ይሆናል። የካርቦናይዜሽኑ ጊዜም እንደ እንጨቱ ብዛትና አይነት ይወሰናል።

ጥሩ ከሠል የሚባለው ክብደት ያለው፣ ጭስ አልባ፣ ከተቀጣጠለ በኂላም ረዘም ላለ ጊዜ ወደ አመድነት ሳይለወጥ የሚቆይ (የአመድ ይዘቱ ከ0.5-5.0 በመቶ፡ የውኃ መጠኑም ከ 5 እስከ 10 በመቶ የማይበልጥ)፣ የካርቦን ይዘቱ ከ50 እስከ 95 በመቶ የሚደርስና በሚቀጣጠልበት ጊዜ የማይንጣጣና አነስተኛ ጭስ ያለው ነው፡፡

## 3.2 የከሠል ምርት መጠንና የገበያ ትስስር

እ.ኤ.አ በ2003 በተደረገ የአለም ባንክ ጥናት መሠረት በኢትዮጵያ ከጠቅላላ የኃይል ፍጆታችን ውስጥ ኤሌትሪክ 1 ከመቶ፣ ነዳጅ (ማለትም ቤንዚል፣ ናፍታ፣ ቡታጋዝ) 7 ከመቶ፣ እንጨትና የመሳሰሉት 92 ከመቶውን ይሸፍናሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት ባደረገው ጥናት መሠረት ኢትዮጵያ ከዓለም በከፍተኛ የከሠል ምርት ከሚታወቁ ሶስት ሀገሮች አንዱዋ ስትሆን ቀዳሚዎቹ ሁለቱ ብራዚልና ናይጄሪያ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ በዓለም ከሚመረተው የእንጨት ከሠል ምርት የ8 በመቶ ድርሻ ስትይዝ፣ ብራዚል 11 ከመቶ ናይጄሪያ ደግሞ 8 ከመቶ ያመርታሉ፡፡ በዚሁ መረጃ መሠረት እ.ኤ.አ ከ1993-2002 ባሉት 10 ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ከ 32 ሚሊዮን ቶን በላይ ከሠል እንደተመረተ ተመልክቷል፡፡ ይህም በዓመት 3.2 ሚሊዮን ቶን መሆኑ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ትልቁ የከሠል ፍጆታ ያለው በዋና ከተማዋ በአዲስ አበባ ሲሆን በከተማዋ የከሠል ተፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ይህን ጥናት ጨምሮ በተለያየ ጊዜ የተካሄዱ የዳሰሳ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት የሌሎች ዘመናዊ የኃይል ምንጮች (ኤሌክትሪክ፣ ቡታ ጋዝና፣ ነጭ ጋዝ) ዋጋ መናሩ፣ በአንጻሩ የከሠል ዋጋ ተመጣጣኝ መሆኑና በየመንደሩ በቀላሉ ሊገኝ የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ እ.ኤ.አ በነሐሴ 2004 ዓ.ም. ለ24 ሰዓታት ለአራት ተከታታይ ቀናት በተካሄደው ቆጠራ በየቀኑ በአማካይ 50 ኪሎ ግራም የሚመዝን 42,045 ኬሻ ከሠል አዲስ አበባ እንደገባ ተመዝግቧል፡፡

በሀገራችን ምን ያህል ቤተሰብ በከሠል ስራ ላይ ተሠማርቶ ይገኛል የሚለውን ለማወቅ የመረጃ እጥረት ቢኖርም የሀገሪቱን ዓመታዊ የከሠል ፍጆታ መጠን ስንመለከት (3.2 ሚሊዮን ቶን) ብዙ ቤተሠቦች ከሠልን በማምረት እንደሚተዳደሩ ወይም የኑሮዋቸው መደጎሚያ እንደሚያደርጉትና በሚሊዮን የሚገመቱ ደግሞ በዋና የኃይል ምንጭነት እንደሚጠቀሙበት መገመት ይቻላል፡፡ ከዚህም በላይ ከሠል ከኢትዮጵያ በሕገወጥ መንገድ ከሶማሌ፣ ከአፋርና ከአማራ ክልሎች ወደ ጎረቤት አገሮች እንደሚላክ ብዙ መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡

## 3.3 የከሠል ችግሮች

የከሠል ምርት በህገ-ወጥ መንገድ የሚከናወንና አመራረቱም ብክነት የሞላው በመሆኑ አንድ ጆኒያ ከሠል ለማግኘት ቢያንስ አንድ ዛፍ መቁረጥ እንደሚያስፈልግ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ያለ አንዳች ቁጥጥር ከተፈጥሮ ደን (ነፃ ምንጭ) የሚመረተው ከሠል የብዝኃ- ህይወት መጥፋትን፣ የአፈር መሸርሸርን፣ የዱር እንስሳት መመናመንን፣ የአፈር መከላትን፣ የተደጋጋሚ ድርቅ መከሰትን፣ ብሎም ድህነትን አስከትሏል፡፡ በተለይ አርብቶ-አደሩ ዛሬ ዛሬ ድህነትን ለመቋቋም ከሠል ማስመረትንና ማምረትን አንዱ አማራጭ ማድረጉ የሚያስገርም አይሆንም፡፡

በተገቢው መንገድ በተጠና ፖሊሲ በሚመራ የደን ማኔጅመንት መሠረት በከሠል ኢኮኖሚያዊ ጥቅም (ምርትና ንግድ) ትስስር ውስጥ አምስት ወገኖች መገኘት አለባቸው፡፡ እነዚህም ዛፍ አብቃይ (አምራች)፣ ከሠል አምራች፣ አጓጓዥ፣ አከፋፋይ/ቸርቻሪና ተጠቃሚ ናቸው፡፡ በሀገራችን ከሠል በተፈጥሮ ከበቀለ የደን ዛፍ በነጻ የሚገኝ በመሆኑ ቆራጭ እንጂ አብቃይ የለውም፡፡ ይህ አካሄድ በደን ሀብቱና በገበያው ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ማሳደሩ አልቀረም፡፡

በቂ የአየር ዝውውር በሌለበትና በተዘጋ ቤት ውስጥ ከሠልን በመጠቀም በሚፈጠረውና አድብቶ ገዳይ (silent killer) ተብሎ በሚታወቀው ካርቦን ሞኖ ኦክሳይድ መርዛማ ጋዝ ሳቢያ አያሌ ሰዎች ለተለያዩ የመተንፈሻ አካላት በሽታዎችና (respiratoy diseases) ብሎም ለሞት ይዳረጋሉ፡፡ ይህ መርዛማ ጋዝ በደም ውስጥ በመግባት የኦክስጅንን ቦታ በመሻማትና የኦክስጅን እጥረት በመፍጠር ለሞት ይዳርጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ከከሠል ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለማስወገድ የከሠል ምርትና ገበያ የአምራቹን፣ የነጋዴውን፣ የተጠቃሚውንና የአካባቢን ደህንነት ባገናዘበ መልኩ መደራጀት ይኖርበታል፡፡ ይሁንና እ.ኤ.አ በ1965 ዓ.ም ከወጡት የመጀመሪያዎቹ የደን ሕጎች ጀምሮ በ1980፣ በ1994 እና በ2007 በወጡት ህጎች ውስጥ የከሠል አመራረቱንም ሆነ ገበያውን አቅጣጫ ለማስያዝ የተቀረፀ ህግ አልነበረም፣ ዛሬም የለም፡፡

ከከሠል ምርት ጋር የተያያዙ በጥናቱ ተለይተው የታወቁ ዋና ዋናቹ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፣

- የከሠል ምርት ከመንግስት ወይም በጋራ ከተያዙ የተፈጥሮ ደኖች በነፃ የሚገኝ መሆኑ፣
- በሌሎች ሀገሮች እንደሚደረገው ለከሠል ምርት ተብሎ የሚለማ ሰው ሰራሽ ደን ያለመኖሩ፣
- የከሠል አመራረት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን በኤክስቴንሽን ያልታቀፈ መሆኑና በማምረቱ ሂደት ውስጥም ብዙ ብክነት መኖሩ፣
- ከሠል እንደ አንድ የኢኮኖሚ ክፍል ተቆጥሮ ጥሬ ዕቃውን፣ አመራረቱንና ገበያውን የሚያደራጅና የሚቆጣጠር አካል አለመኖሩ፣
- የከሠል ምርትና ንግድ የፖሊሲ፣ የድርጅት፣ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ስለሌለው አማራጭ የሌላቸው ሰዎች የሚያከናውኑት ዝቅ ተደርጎ የሚታይ ስራ ተደርጎ መቆጠሩ፣
- የከሠል አምራቾች ተደራጅተው የድካማቸው ተጠቃሚ ያለመሆንና የራሳቸው የደን ይዞታ ኖሯቸው በልማቱ መስክ እንዲሳተፉ ያለመደረጉ ናቸው፡፡

## 4. ጠቋሚ የፖሊሲና የተግባር አቅጣጫዎች

የከሠል ምርትን፤ ንግድንና አጠቃቀምን በተመለከተ መንግስት፤ ማህበረሰቡና ግለሠቦች ሊከተሉት የሚገባቸው የወደፊት የፖሊሲና የተግባር አቅጣጫዎች በዋናነት ከላይ ከተጠቀሱት የችግር የሚመነጩ ናቸው፡፡



ሀ) በኢትዮጵያ ከሠል በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ አምራቾችና ነጋዴዎች የገቢ ምንጭ፣ በሚልዮን ለሚቆጠሩ የከተማ ነዋሪዎች ደግሞ የኃይል ምንጭ መሆኑንና ለመጪዎቹ ብዙ ዓመታትም ይህ ሁኔታ ቀጣይ እንደሚሆን በመቀበል ከሠል እንደ አንድ የኢኮኖሚ መስክ በመንግስት በኩል በቂ እውቅና እንዲሠጠው ማድረግ፤

ለ) ዋና የከሠል ምንጭ የሆነው የደረቃማው የደን ሀብት (Dry woodland) አሁን በሚገኝበት ሁኔታ ተጠቃሚ እንጂ አልሚ ስለሌለው ባለቤት ኖሮት የማኔጅመንት ዕቅድ ተበጅቶለት ቢለማ የኃይል ምንጭነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ብዙ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታዎች ሊያመጣ እንደሚችል በመገንዘብ በዘላቂነት ለማልማት የሚረዳ ፖሊሲ፤ ህግና ደንብ መቅረፅ፤

ሐ) ዋናው የከሠል ምንጭ የሚገኝበት ደረቃማው የግራር ደን እጅግ ሠፊ በመሆኑ በመንግስት አቅም ብቻ ሊጠበቅም ሆነ ሊለማ ስለማይችል የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማደራጀት የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት እንዲለማ ማድረግ፤

መ) መንግስት፤ ማህረሰቡና ግለሰቦች በተናጠልም ሆነ በጋራ ለከሠል ምርት የሚያገለግል ሰው ሰራሽ ደን በማልማት ከተፈጥሮ ደኑ በተጨማሪ የከሠል ምንጭ መፍጠር ይገባል፡፡ ይህ የተፈጥሮ ሀብቱን ከመጠበቅና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቹን ከማሳደግ ባሻገር ለብዙ ሺህ ሰዎች ተጨማሪ የስራ ዕድል ለመፍጠር ይረዳል፤

ረ) ከእንጨት ውጪ ለከሠል ምርትነት በጥሬ ዕቃነት የሚያገለግሉ ሌሎች ተረፈ-ምርቶችን ለመጠቀም የሚያስችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣ ማስፋፋትና ማገዝ፡፡ እንዲሁም ዘመናዊው የኃይል ምንጭ አቅርቦቱ ተሻሽሎ መካከለኛ ገቢ ላለው የሕብረተሠብ ክፍል በበቂ ሁኔታ የሚደርስበትን ሁኔታ መቀየስ ያስፈልጋል፡፡

*መላኩ በቀለ እና ዘነበ ግርማይ*


<u>*ምንጭ*</u>:- Melaku Bekele and Zenebe Girmay ***"Reading through the Charcoal Industry in Ethiopia: Production, Marketing, Consumption and Impact of Charcoal"*** FSS Research Monograph No. 9. 2013.



<u>ምስጋናና ማሳሰቢያ</u>

ይህ ሠነድ የታተመው ከሲቪል ሶሳይቲ ድጋፍ ፕሮግራም አስቸኳይ ተቋማዊ ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የተመራማሪዎቹ ሲሆን በምንም ሁኔታ የድርጅቱን አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም፡፡



**አድራሻ:- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) ✵ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ✵ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

**ስልክ: 011-629 78 88/91 ✵ ፋክስ: 011-629 78 89 ✵ ኢሜይል:** fss@ethionet.et **✵ ድረ ገፅ:** www.fssethiopia.org